# “ግንቦት 7ቶች መጽሃፋቸውን ‘ናቸው’”

ኢትዮጵያዊያን የገጠመንን አበሳና እየገባንበት ያለውን መቀመቅ በማስረዳት የመጀመሪያውንና ዋና ዋና ጉዳዮችን የዳሰሰ፣ ነገር ግን እጥር ምጥን ያለና፣ ስጋት የለቀቀብኝ፣ ተስፋም ያጫረብኝ መጽሃፍ ቢኖር የዶ/ር ሰለሞን ይርጋ “ህልውና” ነበር። ኢትዮጵያዊያን የበሽታ፣ ህዝብ ብዛት፣ የትምህርት ቀውስ፣ ችጋር … ወዘተ በአጠቃላይ የከፋ ድህነትና ኋላ ቀርነት በዘር ፖለቲካ ሲታሽ ወዴት እየሄድን እንዳለን የተዘገበበት ነው። ተስፋው ደግሞ፣ ደራሲው በዚሁ መጽሃፉ ያቀረባቸው የመፍትሄ ሃሳቦች፣ ከገባንበት አዘቅት ለመውጣት የሚያስችል ራእይና ችሎታውም ያላቸው ሰዎች ያሉን መሆናችን ነው።

ሁለተኛውና በድርጅት ስም የታተመው መጽሃፍ የግንቦት 7ቱ “ነጻነት ፍትህ ዲሞክራሲና አንድነት” ነው። በመጽሃፉ ቅርጽ ላይ፣ ለምሳሌ ደራሲው (ግንቦት 7[1])፣ አልፎ አልፎ ረጃጅም አረፍተ-ነገሮችን በመጠቀሙ፣ አንዳንዴ እንደገና ተመልሼ ማንበብ የሚያስፈልገኝ መሆኑ … እና ወዘተ በመሳሰሉትና ኢምንት በሆኑ ጉዳዮች ላይ ማተኮር፣ ስሜቴን ወጥሮ በያዘው በይዘቱ ላይ የምናውለውን ጊዜ ይሻማብናልና ወደ ይዘቱ።

ከገባንበት የታሪክ አጣብቂኝ አኳያ ድርጅቱ በ210 ገጾች ብቻ በተካተቱት ምእራፎች ውስጥ ሊያነሳቸው የሚገባቸውን ጉዳዮች ሁሉ ዳሷቸዋል። አብዛኛው የጽሁፉ ክፍል በመፍትሄ ላይ ያተኮረ መሆኑና መፍትሄውንም ያየበት ማእዘን፣ ባለፉት ሃያ ምንትስ አመታት ውስጥ በሃገር ጉዳይ ላይ ከተጻፉት መጽሃፍት ሀሉ የተለየ ያደርገውም ይመስለኛል። በግልጽና በድፍረት ያነሳውና፣ በህልውናችን አደጋ ላይ የሚያጠነጥነው ጽሁፍ ደግሞ በመጠን ጥቂት ቢሆንም ከስጋትም አልፎ ብርክ ያስይዛል። በመሆኑም መጽሃፉ ያተኮረባቸውንና እኔንም ስሜቴን ወጥረው የያዙኝን ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች አነሳለሁ። መጽሃፉ፡-

1. የመለስ አገዛዝ እያደረሰ ያለውን ግፍና በደል ሳይሆን፣ ግፍና በደሉ የሚያስከትለውን መዘዝና ያለንበትን አደጋ በአጽንኦት ይነግራል።

2. የመለስን አገዛዝ በማውገዝ ብቻ ሳያበቃ፣ እያንዳንዳችን እንደ ኢትዮጵያ ማህበረሰብ አባል ራሳችንን እንድንመረምር የሚያደርገንም ነው።

እነዚህን ሁለት ጉዳዮች ለማስረገጥ ያህል አደባባይ የወጣውንና፣ ሞልቶ ከፈሰሰው የአገዛዙ ግፍና በደል አንዳንዱን እንዲህ እለዋለሁ፡-

- የመለስ አገዛዝ ለመግደልም የ‘ሎተሪ እጣ የሚያወጣ’ መንግስት ነው። በ1997ቱ ምርጫ ለ“ፖለቲካ ፍጆታ” ሲባል፣ ሌላው የአጋዚና ፖሊስ ሰራዊት አባል በሰልፈኛው ላይ የቁጣ መአቱን እንዲያወርድ ስለተፈለገ እና ህዝቡን በግድያው አስደንግጦ ወደ ነበረበት

---

*1 “ኢትዮጵያ” እንዲሁ ቃል ነው—ስም ብቻ። መገለጫው በውስጡ የሚኖረው ህዝብ ነው። ግኡዙ ሜዳ፣ ዉሃና ተራራው ብቻ አይደለም (ይህን ከአቶ መለስ ዜናዊ የተማርኩት ነው። ለኛም ለግኡዙም አልበጁንም እንጂ። እኛን በችጋር፣ በሽብርና በፍርሃት ቆፈን ቀስፈው ይዘውናል፤ ግኡዙንም መሬትና ውሃ እየሰፈሩ ያድሉት ይዘዋል) ። ባጭሩ መጽሃፉም ሆነ ድርጅቱ ግንቦት 7 የሚገለጸው በውስጡ በተሰባሰቡት ሰዎች ነው፤ ሰዎቹ በሚሰሯቸው፣ በሚናገሯቸውና በሚጽፏቸውም ነው—ድርጅቱ የሚመዘነው።*

ለመመለስ፣ እነ አቶ መለስ ሰበቡን *(በሶሻሊስት ቋንቋ 'ነባራዊ እውነታውን*[2]*'* *'objective reality')* ራሳቸው በመፍጠር፣ በህቡእ የሚገድሉ ሰዎችን በማሰማራት፣ እንደ ሎተሪ 'እጣ እየወጣላቸው[3]' ስለተገደሉት ፖሊሶችና ሰልፈኞች አንብበናል።

- በ1970ዎቹ መጀመሪያ፣ እነ አቶ መለስ በረሃ እያሉ፣ በሃሳብ የተለዩዋቸውንና መሃል አገር ይኖሩ የነበሩ የትግል ጓዶቻቸውን፣ የደርግን እጅ ካራ አስይዘው እንዴት እንዳረዷቸው ሰምተናል።
- በትግራይ እስር ቤት ውስጥ በአላማ የተለዩዋቸውንና በግዞት ያሰሯቸውን የትግል ጓዶቻቸውን፣ ተስቦ በሽታ የገባ መሆኑን ነግረው 'በሽታውን ለመከላከል ነው' በሚል፣ በቴትራሳይክሊን-መሰል 'ካብሱል' ውስጥ የሳይናይድ መርዝ ጨምረው ሰጥተው ስለገደሏቸውስ ሰዎች *(በ1980ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ በኢትዮጵያ ሬድዩ የሰማሁትን እንዳለ ቃል በቃል ማስታወስ ባልችልም፣ ጠቅላላ ሃሳቡ ግን ይኸው ነው)* ከደርግ ውድቀት አንድ ወይም ሁለት አመት በፊት ሰምቶ የሚያውቅ የለም?
- በቅርቡ 'የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ሲያደርጉ ተደረሰባቸው' ተብለው በታሰሩት ጄኔራል ተፈራ ማሞ ላይ 'ንብረቱ ሰለተወረሰ በብስጭት ራሱን ከግድግዳ ጋር ሲያጋጭ አይኑ ጠፋ' አይነት ጨካኝ የፍትህ ቀልድ የሚቀልድ የፖሊስ ቃል አቀባይ፣ አቃቤ-ህግ፣ እና ይህንኑ ተቀብሎ የሚያስተጋባ ዳኛ ... የ'ፍትህ' ተቋም ባለባት አገራችን ውስጥ፣ ለወደፊት የሚያስከትለው መዘዝ ምንድን ነው?
- ሚቿ ወ/ሮ አማረች ገላኔ ምንም የፖለቲካ ተሣትፎ እንዳልነበራቸው፣ ካድሬው በቪ.ኦ.ኤ. ቃለ መጠይቅ ወቅት ነግረውናል። የሚች ባለቤት ደግሞ ባለቤታቸው የመኢአድ አባል የነበሩ መሆናቸውን እና ግድያውም ፖለቲካዊ መሆኑን በዚሁ ሬድዮ ነገሩን *(የቪ.ኦ.ኤዋን ጋዜጠኛ አመሰግናለሁ። አደባባይ ያልወጣውን የአገዛዙን ግፍና በደል ደግሞ ቤቱ ይቁጠረው)።* ከወ/ሮ አማረች ሞት በላይ አስደንጋጩ ነገር፣ በሌላ ታጣቂ ገፋፍተው ያስገደሏቸውን የስድስት ልጆች እናት የሆኑትን ሴት፣ ከገዳይ ጋር 'የፍቅር ግንኙነት እንደነበራቸው' እና ለሞታቸውም ምክንያት ይኸው መሆኑ በተነገራቸው የሚች ባለቤትና ልጆቻቸው፣ ወዳጅ ጎረቤትና አጠቃላይ ህዝብ አይምሮ ውስጥ የሚያሳድረውን የተስፋ መቁረጥና ከሰብአዊነትና ፍትህ አንጻር የመለስ መንግስት ወዴት እየወሰደን እንዳለ ስናስበው ይህ ካላስደነገጠን፣ የመለስን አገዛዝ ትተን ከራሳችን ጋር ነው መፋጠጥ ያለብን።

---

*2 "ነባራዊ እውነታ" ማለት፣ ለምሳሌ ለአንድ አመጽ መጀመር፣ በቅድሚያ በህዝብ ላይ የሚደርሰው ጭቆና እያደር እየበዛ፣ የህዝብ ቁጣ እየተብላላና እየጨመረ ሲሄድ፣ ነባራዊው እውነታ ለህዝባዊ አመጽ ፈቀደ ማለት ነው። መለስና ጓደኞቹ ነባራዊው ሁኔታ ራሱ በሂደት እስኪመጣ አይጠብቁም፣ ራሳቸው ማምጣት ይችሉበታል፤ ህዝብን ለማነሳሳት ልክ ሓውዜን ላይ እንደሆነው ማለት ነው።* *http://www.ethiomedia.com/course/telat_ena_ethiopia.pdf*

*3 የሞት ሎተሪ እጣ' ያልኩት "randomly" የሚለውን ቢተካልኝ ብዬ ነው። የሎተሪ እጣ (ዘመናዊውም ሆነ የዘልማዱ ሎተሪ) ከእጅ የገባውን ቁጥር/እጣ እንደሚያወጣ ሁሉ፣ የመለስ አገዛዝ አልሞ ተኳሾችም እነዚያን የ1997 ቅንጅት ሰልፍ ወቅት የተገደሉትን ፖሊሶች ሲገድሉ፣ ምንም መመዘኛ ሳይኖር እንደ እጣ ሁሉ አይናቸው ላይ የገባውን፣ አለያም "አይ ያን ረጅሙን ይሻላል፣ የለም ... ያን ጠይሙን..." እያሉ የገደሉዋቸው ነው የሚመስለው።*

የወ/ሮ አማረች ገላኔ ገዳይ፣ ተራ የፍትህ ቢሮ ዘበኛ መሆናቸው ነው የተነገረው። እኚህ ገዳይ ወ/ሮዋን ሲገድሉ፣ በስራቸው ላይ ከመቆየትና ካለመቆየት ጋር፣ *(ምናልባትም ልጆችም ያሏቸውና የቤተሰብ ሃላፊ ሆነው)፣* ከራሳቸው እና/ወይም ከቤተሰባቸው ህልውና ጋር አስታከው፣ ካድሬው/ካድሬዎቹ ሰውየውን (ገዳዩን) የተጠቀሙባቸው መሆኑን ከመገመት በቀር ሌላ ምን አይነት ምክንያት ሊኖር እንደሚችል አይገባኝም። አደገኛውም ጉዳይ ይሄ ነው።

የመለስ መንግስት፣ ደጋፊ ለማብዛት ያለ የሌለን የህዝብ ሃብት ለካድሬ እና ደህንነት ሰዎች ‘መግዣ’ አድርጎታል። ክፍያው በቀጥታ ጥሬ ገንዘብና ስራ ከመስጠት ጀምሮ ከፍተኛ ትም/እስከመመደብ የሚያደርስ ሲሆን፣ የሚሰጣቸው የ“ስራ ድርሻ” ደግሞ፣ የድጋፍ ሰልፍ ከመውጣት ጀምሮ እስከ ‘የሞት ሎተሪ እጣ’ የወጣለትን ሰው እስከመግደል ይደርሳል።

ይህ ሁለት ጠርዝ ያለው አደጋ ነው። ባንድ በኩል ሊወደሱና ሊሸለሙ የሚገባቸው፣ (የቅርቧ ምሳሌ፣ ወ/ሮ አማረች፣ አቶ አረጋዊ ወዘተ፥… ለፍትህ እና ላመኑበት ነገር ጸንተው የቆሙ በፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊው ጉዳዮች ጥሩ ሰብእናና ብቃት ያላቸው) ዜጎች እየተገደሉ፣ እየታሰሩ፣ ከስራ እየተባረሩና እየተሰደዱ ነው።

በተቃራኒው፣ በፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊው ጉዳዮች ሁሉ ለሀገርና ወገን የሚበጅ ሀሳብ፣ ችሎታውና መልካም ሰብእና ያላቸውን፣ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲባል፣ በግልጽና ባደባባይ ከስራ የሚያፈናቅሉ፣ የሚያሰቃዩና የሚገድሉትን ይሾማል ይሸልማል። የነሱ (የመለስ አገዛዝ) እጅ የሌለበት ለማስመሰል፣ ሌላውን ሰው በእጁ ቢላዋ አስይዘው የሚያርዱ ስዎችን እያሰለጠነ እያሰማራብን ነው። *(ያኔ ገና “ማግብት” ሲመሰረት በደርግ እጅ ያስገደሏቸው የመሃል አገር ጓደኞቻቸው፣ የሀውዜን ገበያተኛ እልቂት፣ የሀየሎም ሞት፣ በቅርቡ ያስገደሏቸው ወ/ሮ አማረች… የዚሁ መሰሪ ስልት ሰለባዎች እንደሆኑ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ተገልጿል)።* የመለስ አገዛዝ ዛሬም ይህን የመሳሰሉ ግድያዎችን ለመፈጸም የማይሰቀጥጣቸው፤ ይኸንኑ ሲዶልቱና ሲዘይዱ ውለው የሚያድሩ “ሰዎች”ን እየፈለፈለብን ነው።

በ1997 ቅንጅት ሰልፍ ላይ እንደ ሎተሪ ‘እጣ ወጥቶላቸው’ (randomly) የተገደሉት ሰልፈኞችና ፖሊሶች፣ በጅማ መስጊድ ውስጥ እንደ ቄስ የለበሰ ሰው ልኮ ማስገደልና ማጋደል፤ በተቃራኒው እንደ ሙስሊም የለበሰ ሰው ቤ/ክ ውስጥ ልኮ ማስገደልና ማገዳደል፤ ያኔ ከተቃዋሚ መሪዎች ጋር በእግሩ ሲጓዝ የታዘባቸው አሜሪካዊ ዲፕሎማት (በዲፕሎማቱና በተቃዋሚ መሪዎቹ ላይ ምራቁን የተፋው ካድሬ/ደህንነት)፣ በግፍ በታሰሩት ጄኔራል ላይ “…ተናዶ ግድግዳ ጋር ሲጋጭ አይኑ ጠፋ…” ብሎ ለማሾፍ የማይመለስ ምስክር፣ ፖሊስ፣ አቃቤ-ህግና ዳኛ… ወዘተ “ወያኔ በፍትህ ላይ የሚያደርገው ማላገጥ እንደሰው በማህበረሰብ እንድንኖር ያደረጉንን የሞራል መሰረቶቻችንን እየናደ ነው…” (ገጽ 72)። እንዲህ አይነት ኢ-ሞራል የሆኑ ድርጊቶች እየበዙና ፍትህ እየተረገጠ በሄደ ቁጥር፣ የመለስ አገዛዝ እየዘራ ያለው አደገኛ መርዝ “… ስርአት አልበኛነትን በማስፈን ማህበረሰባችንን ማውደሙ ብቻ ሳይሆን እንደሰው ክቡር ናቸው ያልናቸውን መለያዎቻችንን በማጥፋት በአውሬ ደረጃ ዝቅ ያደርገናል…” (ገጽ 72)።

አብዛኛው ሰው የሚስማማበት አንድ ጉዳይ ዛሬ በወያኔ ስር የተሰባሰቡት ደህንነትና ካድሬዎች ብዙዎቹ፣ ከስራ ምርጫ ማጣትና የእለት ጉርስ ለማግኘት እንደሆነ ነው። ማናችንም ማወቅ

የሚገባን የመጀመሪያ ነገር አለመራብ ሰብአዊ መብት ነው። መራብን መፍቀድ ራሱ ራስን ከሰውነት ማውረድ ነው። እልፍም ሲል፣ በልቶ ለማደር ሲል ሌላውን የሰው ልጅ የሚያስርና የሚገድል 'ሰው'፤ ከላይ እንደተጠቀሰው፣ እንደሎተሪ 'እጣ ወጥቶላቸው' በ1997ቱ የቅንጅት ሰልፍ ላይ የተገደሉት ፖሊሶች *(እነዚህ ፖሊሶች፣ ህዝቡ ጋር አብረው ሰልፍ የወጡ አለመሆናቸውን አንባቢዬ አሁንም በሃሳቡ ይያዝልኝና)*፣ እንዲገደሉ ያቀዱትም ሆኑ ግድያውን የፈጸሙት *(ካድሬ፣ ደህንነቱና ታጣቂዎቹ)*፣ 'ይቺ የዋህ በግ ምን አደረገችኝ? ይልቁንም ተኩላ ተንኮለኛ ናትና በጓን ትቼ ተኩላዋን እበላታለሁ…' ብሎ ሳይለይ ከሚባላው ጅብ በምን ይሻላሉ?

የመለስ መንግስት የአገዳደሉ ክፋትና መሰሪነት የሚረብሽ ከመሆኑ በስተቀር፣ በደርግም ጊዜ ከቀይ ሽብር ጀምሮ *(ቀይ ሽብር ለነጭ ሽብር አጸፋ መሆኑንም ሳንረሳ)* እስከ ነጻ እርምጃ ድረስ አሰቃቂ ግድያዎቹን አይተናል። እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የደርግና የመለስ መንግስት የግፍና የጭካኔ ድርጊቶች፣ እንደ ህዝብ በሰብእናችን ላይ ያሳደሩትና ወደፊትም የሚያሳድሩትን ጫና በተመለከተ በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ ግለ-ሰቦች በተለያዩ ጽሁፎች የዳሰሷቸው ቢሆንም እንደ ግንቦት 7 በጥልቀት የገባበት ግን ያለ አይመስለኝም። የመለስ መንግስት እያደረሰ ያለው ግፍና በደል፣ በጥቂት ግለ-ሰቦች እና/ወይም ቡድን አባላት ላይ ከተፈጸመ በደል ባሻገር ነው። እየሆነ ያለው፣ በአጠቃላይ በትውልድ ላይ እየተከሰተ ያለ 'የሰብእና መራከስ' ነው።
"… በደርግ ዘመን የሚሞተው ሰው ብቻ ነበር። በወያኔ ዘመን ግን የሚሞተው ሰው ብቻ ሳይሆን በሃገራችን ህዝብ ባህልና ስነልቦና ውስጥ ለዝንተአለም የኖረው የፍትህ ትርጉምና ህዝብ ለፍትህ ያለው ቀናኢነት ጭምር ነው።…" (ገጽ 59)።

&&&&&&&&&&&&&&&

ከምሰራበት መ/ቤት ካለ ክበብ፣ ምሳ ላይ አልፎ አልፎ የሚመጣ አንድ የ1ኛ ደረጃ ትም/ አስተማሪ አውቃለሁ። ከርሞ ከርሞ ሲመጣና "ምነው ጠፋህ?" ስለው "ወዳጄ፣ በወርም በሁለትም ወር እንደምንም ተሚሙቼ *(ቆጥቤ ማለቱ ነው)* አንዳንዴ የምመጣው በክበባችሁ ምሳ ለመቀናጣት ነው። አለዚያ ራቴ ሁሌም ጉልት ነው" ነበር የሚለኝ። ጠፍቶ ከርሞ፣ ከጥቂት ሳምንታት በፊት ምሳ ላይ ተገናኘንና፡ "የመማር ማስተማሩ ሂደት እንዴት ነው?" አልኩት፤ እንደ ቀልድ።
"ማስተማር ድሮ ቀረ" አለኝ። እንደልማዱ የኑሮ ውድነቱንና የትም/ፖሊሲውን እያማረረ መሆኑን በመገመት ዝም አልኩ።
"'ምነው?' አትለኝም?" አለኝ።
"ምነው?"
"ምግብ ሳይበሉ እየመጡ አይምሯቸውን እየሳቱ የሚወድቁ *(ኮላፕስ የሚያደረጉ)* ልጆችን ማንሳት ሆኗል ስራችን" ነበር ያለኝ።

&&&&&&&&&&&&&

"ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየውን የሰብእና መራከስ፣ ውርደትና አሰቃቂ ድህነት እያየን እንዳላየን ማለፍ የምንችለው ቀደም ብለን እራሳችንን ከሰውነት አውርደን በእቃነት ለማስቀመጥ በመቻላችን ብቻ ነው። ራሳችንን በእቃነት ለማስቀመጥ ፍላጎቱ እስካለን ድረስ ደግሞ በእቃነት ሊያስተናግዱን ዝግጁ የሆኑ ሌሎች ሰዎች ሁሌም እንዳሉ መረዳት ይኖርብናል። መብታችንን ከሚገፉት በላይ መብታችን በተለያዩ ምክንያቶች እንዲገፈፍ የፈቀድነው ግለሰቦች ነን በቅድሚያ ተወንጃይና ተወቃሽ መሆን የሚገባን። ከግል ሰበብ አንስተን በባህልና በማህበረሰብ ከወረስናቸው

ዝንባሌዎች ጭምር አንዳቸውም ለነጻነታችን ላለመታገል ምክንያት መሆን እንደማይችሉ ግን እናውቃለን” (ገጽ 28)።

መጽሃፉ ጣታችንን መለስ ላይ ከመቀሰር አልፈን፣ እንደ ህብረተሰብ አባል፣ እያንዳንዳችን ራሳችንን እንድናይ በሚያስችል መልኩ የተጻፈ መጽሃፍ ነው። “… ነጻነትን ያህል ሰው የሚያደርገንን ታላቅ ጸጋ አስገፍፈንና ተገፈን ምንም እንዳልሆንን አስመስለን ለማለፍ እንሞክራለን። ችግሩ ግን የነጻነት ጉዳይ የምርምርና የጥናት ውጤት ሳይሆን ሰው ሆኖ ከመፈጠር ጋር የተያያዘ እርግማን በመሆኑ ሁላችንም እራሳችንን እያጭበረበርን እንደሆነ እናውቀዋለን። የነጻነትን ጉዳይ ፍርፋሪ እየለቀመ በውርደት የሚኖረው የኔ ቢጤ ያውቀዋል። የወያኔ ጌቶቹን አይንና ጆሮ ፈርቶ የሚኖረውም የዩኒቨርሲቲ አስተማሪ ያውቀዋል። ‘እኔ አንድ ድሃ የእግዜር ለማኝ ነኝ ምን ማድረግ እችላለሁ?’ የሚለው ድሃ በውስጡ የሚንቀለቀለውን በነጻነትና በእኩልነት ሰብእናው ተከብሮ እንዲኖር ያለውን ማምለጫ የሌለውን ሰብኣዊ ፍላጎቱን ቢፈልግ እንኳን ማጥፋት አይቻልም። ከዚህ ፍላጎት መሸሽ ካልሆነ ማምለጥ አይቻልም። በተመሳሳይ ‘እኔ የፖለቲካ ሰው አይደለሁም፤ ሳይንቲስት ነኝ፤ ኢኮኖሚስት ነኝ፤ ሃኪም ነኝ፤ ቄስ ነኝ፤ አርቲስት ነኝ፤ ነጋዴ ነኝ፤ የሚለው ዜጋ የነጻነቱን ጉዳይ የፖለቲካ ሰዎች ስራ አድርጎ ሲተወው የሚሰራውን ያውቃል። እራሱን ለገዛ ነጻነቱና ሰብእናው ከመታገል እያሸሸ እንደሆነ ያውቃል። ‘ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ’ ነውና ለራሱ እየቀጠፈ እንደሆነ ይገባዋል። ምክንያቱም ጋዜጠኛው ‘እውነት አትጻፍ’ ሲባል፣ ነጋዴው ‘ጫማ ስመህ፣ ጉቦ ሰጥተህ እቃህ ከጉምሩክ ይለቀቃል’ ሲባል፣ ፕሮፌሰሩ ‘ተማሪዎችህ እኛ ከፈቀድነው ውጭ ጥያቄ ማንሳት፣ ውይይት እንዲያደርጉ ማድረግ አትችልም’ ሲባል፣ ተማሪው ‘ለከፍተኛ ትምህርትና ስራ ለመቀጠር የመለስ ዜናዊ ጀሌ የግድ መሆን አለብህ’ ሲባል፤ አንድ ዜጋ በዘሩ እየተለየ ጥቃት ሲደርስበት፣ በእምነቱ የተነሳ ሲዋረድ፣ እየተገፈፈ ያለው ከሰብእናው ጋር የመጣውን ነጻነቱን ነው። ከነጻነቱ ጋር የመጣውን ሰብእናውም ነው። ይህን አይነቱን የነጻነት ማስከበር ስራ ለፖለቲከኞች መተው የሚቻለው ራስን በከፍተኛ ማጭበርበር በመሙላት ብቻ ነው። በሃገር ውስጥም ሆነ ከሃገር ውጭ በእንዲህ አይነቱ የራስ ማጭበርበር የተሞላ የውሸት ህይወት የምንኖር ብዙዎች ነን…” (ገጽ 23 & 24)።

መጽሀፉ ካሰፈራቸው እጅግ በርካታ ቁም-ነገሮች ውስጥ፣ ካንጀቴ የገባውንና ግንቦት 7 ውስጥ የተሰባሰቡትንም ሰዎች ማንነት ይነግርልኛል ያልኩትን ጠቅሼ ጽሁፌን ላጠቃልል። “ሰውን ቁሳዊ ምቾት ብቻ አያኖረውም። ማህበራዊና መንፈሳዊ ምቾቶችንም ይፈልጋል። እንዲያውም የሰው ልጅ ራሱን ባበቃ (ባሳደገ) መጠን፣ ለማህበራዊና መንፈሳዊ ምቾቶች ያለው ክብር እየበዛ፣ ለቁሳዊ ምቾቶች ያለው ክብር ደግሞ እየቀነሰ ይሄዳል…” (ገጽ 32)። በቅርቡ አንዱ የአውራምባ ጋዜጠኛ፣ የልብ ህክምና ባለሙያውን ዶ/ር በላይ አበጋዝን ‘በጣም ሊመሰገኑ ይገባዎታል…’ ቢላቸው “… በህይወቴ ላደርገው የፈለግሁት ነገር ሲሳካልኝ፣ ደስታንም ሆነ የሰላምን እንቅልፍ ያገኘሁትም የተጠቀምኩትም እኔ ራሴ፣ ለእኔ ምን ምስጋና ያስፈልገኛል…?’ አይነት አባባል ነበር የተናገሩት።

አንባቢዬ የዶክተር በላይን ማህበራዊና መንፈሳዊ ምቾት እኔ ባየሁበት አይን ካየልኝ፡-

1. ግንቦት 7 ውስጥ የተሰባሰቡት ሰዎች፣ ብርቱካን ሚደቅሳ፣ በመለስ ካድሬዎች እጅ የተገደሉት አቶ አረጋዊ፣ ወ/ሮ አማረች እና ሌሎችም የሚታወቁና የማይታውቁ)፣ በአገር ውስጥና በውጭ፣ በትጥቅም ሆነ በሰላማዊ ትግል ከልባቸው አምነው

የሚታገሉት … ወዘተ ሁሉ፣ በፖለቲካው *(የጤናው፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊው ችግሮቻችን ሁሉ ቁልፍ በሆነው)* መስክ ተሰማርተው፣ ለእኩልነት፣ ለፍትህ እና ሰላም የቆሙ፣ ከቁሳዊ ምቾት ይልቅ፣ ማህበራዊና መንፈሳዊ ምቾትን የመረጡ ናቸው።

2. የመለስ አገዛዝ ደግሞ በተቃራኒው፣ እንደዚህ ያሉ ሰብእና ያላቸውን ሰዎች እየገደለና እያሰረ፣ ለቁሳዊ ምቾት ሲሉ፣ ሰውን 'የሚበሉ' *(እላይ የጠቀስኩትን ጅብ አስቡልኝና)* ሰብአዊነታችንን እየተፈታተነና ህገ-አራዊትነትን እያሰፈነብን ነው።

የመለስና ጓደኞቹ መሰሪና በክፋት የተሞላ አገዛዝ በተራዘመ ቁጥር፣ ቁልቁለቱን እየተንደረደርን እየወረድን እንደሆነ ነው የሚሰማኝ—ወደ ፍጹም ስርአተ-አልበኝነትና ይኸው ወደሚያስከትለው ምስቅልቅል። ግንቦት 7፣ የ'ሆብስ'ን ህገ-አራዊትነት የሰፈነበትን የቅድመ-ህብረተሰብ ዘመን ህይወት ጠቅሶ (ገጽ 65 እና 66) … እየሄድንበት ያለውን መንገድ መዳረሻ አስፈሪነት ደጋግሞ ሲነግረን የተጋነነ አይመስለኝም። ለዚህም ነው ከመዘግየቱ በፊት በማናቸውም መንገድ የመለስን አገዛዝ እድሜ፣ በትጥቅም ቢሆን፣ ግን ደግሞ በከፍተኛ ጥንቃቄ፣ ማሳጠር የሚያስፈልገው።

ለዚህ እውን መሆን ደግሞ፣ የመለስን መንግስት ከመርገም ወይም ከማውገዝና 'ብርቱካንን አሰረ'፣ 'መሬት አስቆረሰ'፣ 'ወደብ አስወረስ'፣ 'ሰው ገደለ/አስገደለ' …ወዘተ… እያሉ በየቡናው ከማውራት በላይ በተለያዩ አመጾች መሳተፍና፣ ይህም ባልተቻለባቸው ሁኔታዎች፣ በሃሳብ፣ በቁሳቁስ፣ በገንዘብም መሳተፍ ያስፈልጋል።

አብዛኞዎቻችን ኢትዮጵያዊያን፣ የሌላውን ሰው/ቡድን መጥፎነት በመንገር ብቻ የራሳችንን ጥሩነት *(በተግባር ምንም ጥሩ ስራ ሳንሰራ)* ለማሳየት የመፈለግ በሽታ ያለብን ይመስለኛል። ስንቱ ሰው ታዝቦ እንደሆነ ባይገባኝም፣ አሁን በያ ሰሞን፣ በአቶ ሰለሞን ተካልኝ መጥፎ ሰብእና ላይ በተጻፈ አንድ ጽሁፍ እና ሁሌም በቅን ሃሳቡና  በጥረቱ የማደንቀው ፕሮፌሰር አል-ማርያም በዚያው ሰሞን በጻፈው ጽሁፍ ስር ከአንባቢያን የተሰነዘሩ አስተያየቶችን በአይነት እና ብዛት መመርመር ማንነታችንን ይነግር ይመስለኛል *(የመለስ አገዛዝ የድረ-ገጽ ካድሬዎች/ተዋጊዎች 'cyber warriors' የሚሰጧቸውን አስተያየቶች [አንዳንዴም ከተራ ብልግና ያልዘለሉና፣ ለምሳሌ የትግራይን ህዝብ መደበቂያ ለማድረግ "…እነዚህን ቅማላም ትግሬዎች…" አይነቶቹን] አስተያየቶች ሳይጨምር)*። ለቁሳዊ ምቾት ሲል ራሱን ያወረደው አቶ ሰለሞን ተካልኝ[4] ላይ ያን ያህል የርግማን መአት ከማውረድ ይልቅ፣ ጊዜውን፣ ጉልበቱን፣ ገንዘቡን ሳይቀር ለመንፈሳዊ ምቾቱ ሲል እያዋለ ያለውን ፕሮፌሰር አል-ማርያምን 'አመሰግናለሁ' ብሎ አንዲት መስመር ኢሜል ከመላክ ጀምሮ፣ ሃሳቡን በምንጋራባቸው ጉዳዮች ሁሉ (ለምሳሌ 'ኢሳት'ን በመደገፍ) በገንዘብ፣ በቁሳቁስ እና በሀሳብ መሳተፍ ያስፈልጋል።

---

[4] ዘፋኙ ድሮም አይመቸኝም ነበር። የመለስ አገዛዝ፣ ምስኪኑን አማራ ሳይሆን ይኸን አቀንቃኝ ነበር 'ነፍጠኛ' ማለት የነበረበት። ከድምጹ ጥሩነት በቀር ግጥሞቹ ሁሉ የነፍጥ ናቸው። ለነገሩ የሱ ለዛ አጣ እንጂ፣ ያገሬ አዝማሪ፣ በየጠጅ ቤቱ ለገንዘብና ጠጅ ሽልማት (ቁሳዊ ምቾት) ሲል መልከ-ጥፉውን ሁሉ ለዛ ባለው ግጥም መልክ ሲቀባ አይደለም እንዴ የሚያመሸው? ታዲያ ለቁሳዊ ምቾቱ ሲል "ጃርት ስላስመሰላቸው የቅንድባቸው ውበት" ቢዘምር ምኑ ይገርማል?

ለኔ መንፈሳዊ ምቾት ማለት ከመለኮት (ሃይማኖት) ጋር የተገናኘውን ምቾት ማለት አይደለም። ከሃይማኖት ጋር የተገናኘው መንፈሳዊው ምችት፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ፣ ከሞት በኋላ ካለው ጽድቅ (መንግስተ ሰማያትን ከመውረስ) ጋር የተገናኘው ምቾት፣ እሱ ራስ ወዳድነት፣ መንግስተ ሰማያት ውስጥ በሰላምና ተድላ የመኖር (ለራስ) ጉጉት አለበት—ለዚያውም እውን ለመሆኑ ማንም ላልመሰከረለት መንግስተ ሰማያት። ግንቦት 7 የሚለውም ሆነ እኔን የገባኝ መንፈሳዊ ምቾት ከዚያ በላይ ነው። በእንግሊዝኛው "virtue leads to happiness" ወይም "do good feel good" የሚለውን አባባል መሰረት ያደረገው ይመስለኛል።

የምእራቡን አለም ሀብትና ስልጣኔ የምንመኘው ከሆነ፣ የእድገታቸው እና ስልጣኔያቸው መሰረቱ፣ ለመንፈሳዊ ምቾት ሲሉ ከጥንት ጀምሮ የሰሩ ሰዎቻቸውን እውቅና በመስጠትና ሃሳባቸውን ዳር ለማድረስ በማገዝ ነው። ዛሬ እጅግ አሰቃቂ ድህነታችን እና ኋላ ቀርነታችን የሚያስቆጨን ከሆነ፣ ለቁሳዊ ምቾታቸው ሲሉ የሚኖሩ (አቶ ሰለሞን ተካልኝ፣ አቶ መለስ ዜናዊ …) የመሳሰሉ ሰዎችን መርገም ብቻውን አይበቃም። ለመንፈሳዊ ምቾት ሲሉ የሰሩ እና የሚሰሩ ሰዎቻችንን እውቅና ከመስጠት (ከልብ በመነጨ አንዲት መስመር 'አመሰግናለሁ' ከማለት እና ለመልካም ስራቸው እውቅና ከመስጠት ጀምሮ፣ የምንጋራቸውን ሃሳባቸውን ለመተግበር ይቻል ዘንድ በሃሳብ፣ ገንዘብ እና ቁሳቁስ ማገዝ ያስፈልጋል።

የ'መንፈሳዊ ምቾት' ሌላው ጥሩ ምሳሌ፣ የዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳ ሰብእና ነው። ዳኛዋ በአቶ ስዬ ጉዳይ ላይ ያን ብያኔ ስትሰጥ፣ ምናልባትም እድገትና እድገቱ የሚያስከትለውን ቁሳዊ (ገንዘብ) ምቾቷን ንቃ መተው ብቻ ሳይሆን፣ ስራዋን ከማጣት ጀምሮ የሚያስከትሉትን እነዚህን ቁሳዊ ችግሮች (እስከ እስራትና ሞትም ቢሆን) ሁሉ ለመንፈሳዊ ምቾቷ ስትል ለመቀበል የተዘጋጀች መሆኗ ነው። እደግመዋለሁ! ምእራባዊያን ዛሬ ለደረሱበት እድገት መሰረቱ፣ በግለ-ሰብ እና/ወይም በቡድን ደረጃ ለመንፈሳዊ ምቾቶቻቸውም ሲሉ በሰሩ ሰዎች ነው። ግንቦት 7 ውስጥ የተሰባሰቡትም መሪዎች ማንነት በዚሁ መጽሃፋቸውና በሌሎች ጽሁፎቻቸውም *(ከተማችን ውስጥ ይታተም በነበረው 'አዲስ ዜና' ጋዜጣ ላይ ይወጡ በነበሩት ጽሁፎችም)* ይገለጽ ይመስለኛል።

መጽሃፉ የመለስን አገዛዝ ሲረግም ብቻ አይውልም። በመሰሪነት የተካነው መለስ ዜናዊ፣ ጓደኞቹና፣ ማንኛውንም የህዝብ ተቃውሞ ለማስቆም ከማቀድ ጀምሮ እስከ መተግበሩ ድረስ አብረውት የሚሰሩት *(ከባለስልጣን ታች እስካለው የደህንነት ሰውና ካድሬ ድረስ ሁሉ)* የኛው የህብረተሰቡ ነጸብራቅ ናቸው። እንዲያውም ለመለስ አይነት አገዛዞች እንዴት 'የተመቸን' እንደሆንንና፣ እንደ ህዝብ ከሞራሊቲ፣ ከሰብአዊነት፣ መቻቻል … ወዘተ አኳያ ብዙ መስራት የሚያስፈልገን ህዝቦች መሆናችንን መጽሃፉ ደጋግሞ ያነሳል። "በሃገራችንና በታሪካችን ተከስቶ የማያውቅ በህዝብ ምስፍና ላይ የቆመ መንግስታዊ የአስተዳደር ስርአት የመመስረት አላማ ማሳካት የሚቻለው፣ በቅድሚያ ተከታታይ የአገዛዝ ስርአቶች የስልጣን እድሜያቸውን ለማራዘም ሲሉ በህብረተሰባችን ውስጥ ተንሰራፍቶ እንዲቀጥል ካደረጉት የጥርጣሬ፣ ራስን ብቻ የማስቀደም፣ እኔ ያልኩት ብቻ ካልሆነ፣ የመሰሪነትና ሌሎችንም ጎታችና ጎጂ ባህሎች ሁላችንም አውልቀን ስንጥል ብቻ እንደሆነ ንቅናቄያችን ያምናል…" ይለናል ግንቦት 7 (ገጽ 115)።

## *ኢትዮጵያዊያን የተሻሉ መሪዎች ይገቡናል።*

Gelanew-Kirar@hotmail.com